## ፓኖራማ ቁጥር 82

## የትዝብት አድማስ

ታህሳሥ 5 ቀን 2002 ዓም

## በተለሙ ያርሿል፥ በጀመሩ ይጨርሿል

ማለዳ ለእርሻ አብረው የተጠመዱ በሬዎች ቀኑ ሲመሽ ከቀንበራቸው አብረው ይፈታሉ። ገበሬው ወደቤቱ ሲገባ በሬዎቹ ወደ ማሳው ተለቅቀው ገለባና ጭድ እንዲበሉ ይደረጋል ። ይህ ሂደት የእርሻው ወራት እስኪገባደድ ድረስ ይቀጥላል ። አብረው የተጠመዱ በሬዎች አብረው እንደሚፈቱ ሁሉ ፥ አብሮ ትግሉን የጀመረው ሁሉ ግን እስከ መጨረሻው ድረስ ትግሉን ይቀጥላል ማለት አይደለም ። መቆየት መልካም በመሆኑ ሁሉን አሳይቷል ። እስከ መጨረሻው በዕምነታቸው የፀኑ ብፁኣን ናቸው ቢባልም፥ ለታሪክ ብፅዕናም ይሁን ለሰውነት ልዕልና የማይቸገሩ ሁሉ፥የጀመሩትን ለመጨረስ የሚቸገሩ አይሆኑም ። በየትግሉ ምዕራፍ እየተንጠባጠቡ ለመቅረት፥የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ ፥ከትግሉ የወጡበትን ሁኔታ ለማስረዳት ይሞክራሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ከሚደርስባቸው የሥነ አዕምሮ ጭንቀት ያላቅቀናል ብለው ለማመን ስለሚፈልጉ ነው። ማነኛውም ሰው የጀመረውን ለምን አልጨረሰም በሚል ብቻ ሊወቅስ-ሊነቀስ ይገባዋል ባይባልም፥ ከሕዝባቸው ጋር የገቡትን ብሔራዊ ቃል ኪዳን በመክዳት በደል ሲፈፅሙ ግን በአርምሞ ሊታዩ እንደማይገባቸው ኅብረተሰቡ አውቆ ሊገነዘብ ይገባል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ በስሙ ሥልጣን ይዞላሁ የሚለውን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ፥ በስሙ እንታገልልሀለን የሚሉትን የፖለቲካ ድርጅቶችንም ጭምር የመጠየቅ፥ የመክሰስ- የመውቀስ ፥የመቃወም፥ የመዋጋትና የመጣል ሙሉ መብትና ሥልጣን እንዳለው ማወቅ ይገባል ። የታሪክ ፍርድም ይሁን የኅሊና ወቅሳ ለጊዜው ባያስጨንቃቸውም ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍርድ ግን ማነኛውም ዜጋ ሊያስጨንቀውና ሊያስፈረው ይገባል ። የአንድ ሀገር ሕዝብ የመጨረሻው ባለሥልጣን መሆኑን ያልተረዳ መንግሥትም ሆነ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ማነኛቸው ተቋማት ሁሉ ፥ መጀመሪያውኑም ባይፈጠሩ ይሻላቸው ነበር ። ድርጅቶች ከመመስራታቸውም በፊት፥ መንግሥትም ከመቋቋሙ አስቀድሞ ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ማወቅ አለባቸው ። ይህንን ታላቅ ትምህርት ሳይረዳ ፥ የፖለቲካ ድርጅት መመስረትና መንግሥት ማቋቋም ማለት ለፖለቲካ ዘማዊነትና ለወንጀል ተግባር ለመሰማራት መዘጋጀት ማለት ነው ። ሁለቱም

አስነዋሪዎች ናቸው ::በመሆናቸውም ባኅርያቸውና ድርጊታቸው በሕዝባዊ አመፅ ይወገዛሉ:: ይወገዳሉ::

የዛሪይቱ ኢትዮጵያ በሁለት በኩል እየተጎዳች ትገኛለች :: የመጀመሪያው ፥ የነበራት ጅዮግራፊያዊ ቅርጿ እየተሸራረፈ በመሄድ ላይ ሲሆን ፥ ሁለተኛው ደግሞ ፤ የፖለቲካ መልክዐ-ምድሯ የተበላሸ መሆኑ ነው:: ሁለቱም ለሀገራችን ጥፋቶች ናቸው :: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ሁለቱንም ዐይኑ እያየ ጆሮው እየሰማ ሊከላከላቸው ፥ ሊቋቋማቸውና ሊያስወግዳቸው አልቻለም :: ከአቅሙ በላይ ሆነውበት ሊቋቋማቸው ያልቻለበት ምክንያት ሁለት ከባድ ጠላቶች ስላጋጠመው ነው :: እነኝህም ፥ የውጭ ባዕዳንና የእነርሱ ቅጠረኛ የሆነው ወያኔ ናቸው :: ለዚህም ነው ታዲያ ዛሬ ፥ ሀገራችን የቅርብ ጉረቤትም ይሁን የእሩቅ ዘመድ የሌላት ሀገር ሆናለች የምትባለው :: የውጭ ባዕዳን ጠላቶቿንም ሆነ የውስጥ ቀበኛዋን በመቋቋም ፥ የሚፈረካከሰውን የጅኦግራፊ ቅርጿን ለማዳንም ሆነ ብልሹ የሆነውን የፖለቲካ መልክዐ-ምድሯን መለወጥ የሚችሉት የራሷ ልጆች በሆኑ ነበር ::ይኽ ግን እስካሁን አልተቻለም :: ይህንን ብሔራዊ ኃላፊነት ተሸክሞ በብቃት መወጣት የሚገባው የተቃዋሚው ጎራ መሆኑን ሁሉም ዜጋ የሚጠብቀው ነበር :: ተቃዋሚው ክፍል ግን ጎራውን አጠንክሮ ተቃዋሚነቱን አስተባብሮ ፥ የወገን አለኝታነቱን አስከብሮ ብሄራዊ ግዴታውን በመወጣት ተልዕኮውን ለመፈፀም አልቻለም :: ይህ አልበቃ ብሎት ፥ በአሁኑ ወቅት በሦስት ረድፍ ተለያይቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሄራዊ ተስፋ በመፈታተን ላይ ነው ::

<u>አንደኛው ቡድን</u> የወያኔን ሥልጣን አምኖ በመቀበሉ ወያኔዎቹ "ህጋዊ ተቃዋሚ" የሚል ታርጋ ለጥፈውለት እንደ ሀረግ-ሬሳ በወያኔዎቹ ታዛ ተንጠላጥሎና ተሽመድምዶ የቀረ ክፍል ነው :: የሀረግ ሬሳ ህይወቱን ለመኖር የሚችለው በመለስ ዜናዊ ፈቃድ መሆኑን አምኖ ተቀብሏል:: የወያኔን አጀንዳ ከማስፈፀም የተለየ ተግባር እንደሌለው በተጨባጭ ያስመስከረ በመሆኑ፥በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከበሬታም ይሁን ተዓማኒነት ተነፍጎታል :: ህይወቱም ወያኔ እስከሚቆይ ብቻ ስለሆነ ይህንን ተገንዝቦ፥ ለመኖር ብቻ ሲል የሚኖር ክፍል ነው :: ይህ ሁኔታ ታዲያ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውነተኛ ወዳጁንና ጠላቱን ለይቶ እንዲያውቅ ዕድል ሰጥቶታል::

<u>ሁለተኛው ክፍል</u> በብሄር የተደራጀውና የኢትዮጵያን ብሄራዊ አጀንዳ እንደ ቅድሚያ አጀንዳው አድርጎ ለማየት የማይፈለገው ክፍል ነው:: አሁን የሚታየው የፖለቲካ መልከዐ ምድር እንዳለ ቢቀጥል ይስማማዋል :: የወያኔን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሂደት የሚያየው ከራሱ የግል አጀንዳ ጠቀሜታ አኳያ እንጅ ለመላው የሀገሪቱ ዜጎች ሁሉ

ይጠቅማል / አይጠቅምም የሚለውን ጉዳይ መጠየቅ ቀርቶ ማሰብም እንኳን አይፈልግም ፡፡ ከወያኔ ጋር አለኝ የሚለው ልዩነት አስተዳደራዊ አለመግባባት ነው ፡፡ ጥቅሜ አነስኝ ወይም ተነፈግሁ ፥ የመዋቅርና የጥገና መስተካከል ይደረግ አይደረግ በሚል ሽኩቻ ላይ ያነጣጠረ ነው ፡፡ ይህ ክስተት ደግሞ ከማንም የበለጠ የጠቀመው ቢኖር ወያኔን ብቻ ሆኗል፡፡ በወያኔ ፓርላማ ተሰብስቦ የወያኔን የጨረባ ተስካር ለማውጣት የሚተራመስ ቡድን በመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እንቅፋት ከመሆን በቀር ርባና የለውም ፡፡ ምን ጊዜም ቢሆን፥አንድ ሎሌ ለሁለት ጌቶቹ በእኩል ታማኝነት ሊያገለግል ከቶ አይሆንለትም፡፡ የወያኔ አሽከር ተሁኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እታገላለሁ ማለት ቀልድ ነው ፡፡ በራስ ላይ መቀለድ !

ከላይ በአንደኛውና በሁለተኛው ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱት ክፍሎች የጋራ ባኅርይ አላቸው፡፡ ሁለቱም፥ ወያኔ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የተጠላ፥ የተናቀ፥ የተነቀፈና የተዋረደ መሆኑን በሚገባ ተረድተውታል ፡፡ ምናልባትም ጊዜው ሲደርስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የወያኔ ሥርዓት እንደሚደመሰስ ይገነዘባሉ ፡፡ በመሆኑም ከወያኔ ጋር አሁን ሰልፋቸውን ያሳመሩት ከፍርሃትና ከጊዚያዊ ጥቅም አንፃር እንጅ ወያኔን ወደውና ሥርዓቱንም ከልብ ተቀብለው አይደለም ፡፡ የጋራ ሰልፋቸውን ያሳመሩት ፥ **አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት** ከሚል የእበላ ባይነት ስሌት ብቻ ነው፡፡ይህ የእበላ ባይነት ባኅርይ ደግሞ ከኅብረተሰብ ታሪክ ጋር የነበረ አሁንም ያለ፥ ወደፊትም የሚኖር ስለሆነ፥ ከስተቱ የሚያስገርም አይደለም ፡፡ የሰውን ልጅ ጠባይና ምግባር ለማወቅ የሚመራመሩ የሥነ ልቦናም ይሁን የሥነ አእምሮ ሊቃውንት እንደሚሉት፥ የእበላ ባይነት ጠባይ ዋና ትኩረቱ ፥ የጊዜን አመችነት በሚገባ እየተረዱ በሁኔታው መጠቀም ነው ፡፡ በፈታኝ ጊዜ አደጋውን ከመጋፈጥ ይልቅ ተመሳስሎ በመቆየት ሁኔታው ሲያመች ደግሞ በሚያስደንቅ ፍጥነት ለአዲሱ ሁኔታና ወቅት እራሱን አመቻችቶ በመቅረብ ለመጭው ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መዘጋጀት ነው ፡፡ ዓላማ ፥ መርኅ፥ ዕምነት፥ ጀግንነት ፥ መሥዋዕትነት፥ ለሀገርና ለሕዝብ ቤዛ መሆን ፥ ታሪክ ፥ ቃል- ኪዳን ፥ የራስን ክብር አስከብሮ የሀገር ክብርን ማስከበር ወዘተ.... የሚባሉት የሰውን ልጅ የሚያስከብሩ ባህርያት አይኖረውም፡፡ እነኝህን ጠባዮች ያዘለ ሁሉ በየትኛውምሥርዓት ለሚመጣ ባለሥልጣን ራሱን እያመቻቸና እንደ ሽንብራ ቂጣ እየተገለባበጠ ይቀርባል ፡፡ በወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ያላቸው ሀገራችንም ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ግለሰቦችና ቡድኖች አመች ሆናለች ፡፡ ወያኔም በመሳሪያነት ይጠቀምባቸዋል ፡፡

<u>ሦስተኛው ክፍል</u> ወያኔን በመንግሥትነት የማይቀበለው ተቃዋሚ ኃይል ነው ፡፡ ይህ ኃይል የዓላማ ብርታት፥ የራዕይ ጥራት፥ የዕምነት ፅናት፥ የአቋም ስፋት፥ የሀገርና የሕዝብ ፍቅር መሠረት ስለአለው፥ በኢትዮጵያዊ ዜግነቱና በብሔራዊ ጥቅሙ ላይ ከወያኔ ጋር ሊደራደር አይችልም፡፡ የወያኔን ሥልጣን እስከ ህገ መንግሥቱ አይቀበለም ፡፡ ዘመን በማይሽረው

ሁኔታ በማይለውጠው÷ የዜጎቿ እኩልነትና አንድነት እንዲሁም÷ በማይገሰሰው በሀገራችን የነፃነት ልዕልናም ይሁን በግዛት አንደነት ላይ የማይደራደረው ኢትዮጵያዊ የአንድነት ጎራ ÷ የጀመረውን መራራ ትግል ከግቡ ሳያደርስ አይበገርም ። የገባውንም ቃል ኪዳን አያጥፍም። ትጥቁን አይፈታም ። “ አይበገሬነትን አክራሪነት ነው ። ” ከወያኔ ጋር መደራደር ግን ብልህነት ነው ። የሚሉ ክፍሎች የሚወስዱትን ውሳኔ የሚተቸውና የሚፈርደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሆነ ÷ የነዚህ ክፍሎች ጉም ገምታ ብዙም ሊያሳስብ አይችልም ። <u>በራሳቸው ድርጊትና ርምጃ ምክንያት በሚደርስባቸው ችግር የተነሳ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚመጣባቸው ተቃውሞ የሚድኑ እየመሰላቸው በዓላማው ፀንቶ የሚታገለውን ኃይል እንደ መሥዋዕት ጠቦት ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ ።</u> ይህ ግን በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በታሪክ ፊት ተቀባይነት የለውም ። ይህንን በሚገባ የተረዳው የአንድነት ኃይል ÷ የጀመረውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ፀንቶ ከመታገል ሌላ ሀገራዊ አጀንዳ የለውም ። ወገንተኝነቱም ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ነው ። የጀርባ አጥንቱ ÷ ጥንካሬና ኃይሉም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ያምናል ። የአይበገሪነት ባኅርዩም የመነጨው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና ባኅል ነው ።የአትንኩኝ ባይነት ምሥጢሩ ይኸው ነው ። ከዚህም የተነሳ÷

**ተኩሰው አይመቱ ወይ ተሟግተው አይረቱ÷**
**የአንበሳውን ደቦል ነካኩት በከንቱ ።**

**እያለ ትግሉን በፅናት ይቀጥላል ። ፍርዱንም ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለታሪክ ይተወዋል ።**